የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)
SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN
POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)

ጥር 7/2002

# ለሰብዓዊ መብት መታገል የዜግነት ግዳጅ ነው

በኢትዮጵያ መሰረታዊ ሰብዓዊ መብቶች ተረግጠው ሕዝብ መከራና ሰቃይን በሁሉም መስክ እየተቀበለ ነው፡፡ በስልጣን ላይ ያለው ቡድን ፀረ ዴሞክራሲ መሆኑ የተጋለጠ ሲሆን ከዓመት ዓመት ደግሞ በሰብዓዊ መብት ረገጣ እየከፋና እያመረረ መሄዱ በዓለም ደረጃም የታወቀ ሆኗል፡፡

ለሰብዓዊ መብት መከበር መታገል የዘሁሉም ዜጋ ግዴታ ነው፡፡ ለሰብዓዊ መብት ሲታገሉ የወደቁትን መዘከር፤ ለእስር የተዳረጉትን መታደግ፤ የእስረኛ ቤተሰቦችን ማገዝ፤ ተይዘው ደብዛቸው የጠፋውን እስረኞች ማስታወስ፤ለአንድ ወይም ሁለት እስረኛ ሳይሆን ለሁሉም የፖለቲካ እስረኞች መጮህ ያስፈልጋል፡፡ ሰብዓዊ መብት ተሸራርፎ የሚታይ አይደለም፡፡ ለአንዱ መብት ተከብሮለሌላው ሊሻር አይታሰብም፤ ተቀባይነትም እይኖረውም፡፡ ስለዚህም ፍትህ በጎደለበት ሁሉ መቃወምና ለሁሉም ዜጋ ሙሉ መብት መከበር መቆም የግድ ነው፡፡ የሁልጊዜ ትግልም ነው፡፡ በቃሊቲ ላሉት ከጮህን በዝዋይ ዴዴሳ፤ አርባ ምንጭ ጅጅጋ ወዘተ ላሉትም የፖለቲካ እስረኞች ድምፃችን መሰማት አለበት፡፡ ከፖለቲካ አቅዋም መመሳሰል መለየት ባሻገር ፍትህ አልባ ለሚፈፀመው በደል ሁሉ ተቃዋሚ ሆነን መገኘት አለብን ማለት ነው፡፡ የእኔ እስረኛ የእኛ እስረኛ የምንለው ሳይሆን የሁላችንም እስረኛ ብለን በጋራ መቃወምና ይፈቱ ጥሪን ማስተጋባት ይኖርብናል፡፡ብርቱካን ሚዲቅሳ ፤አበራሽ በርታና በየማጎሪያው ያሉት ሁሉ ሴት እስረኞች በአስቸኳይ ይፈቱ ማለት አለብን፡፡ ለአንድ ድርጅት አባል እስረኞች ብቻ ሳይሆን ለሁሉም ድርጅቶች አባል እስረኞች ጩኸታችን መስተጋባት ይኖርበታል፡፡

ዛሬ በሁሉም መስክና በሁሉም ቦታ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የሕዝብን መብት በመርገጥ ላይ ነው፡፡ በአርሶአደሩ ላይየሚደርሰው አሰቃቂ በደል ዛሬ ደግሞ መሬቱ ለባዕዳን እየተሰጠበትና ባዕድ በዝባዥ እየተሰየመበት ይበልጥ ተባብሷል፡፡ የሰራተኛው ሕዝብ መብትም እንዲሁ ተሸርሽሯል፡፡ የብሄረሰቡ ጭቆናና ጥላቻ ተፋፍሞ በሕዝብ ላይ በጅምላ በደል እየተፈፀመ ነው፡፡ በጦር ሠራዊቱም ውስጥ ቢሆን አፈና አለ ፡፡ በኤኮኖሚው መስክም የአገዛዙ ጭፍን ብዝበዛ ብዙዎችን ለኪሳራ ዳርጓል፡፡ ለስልጣን ያገዙ ድርጅት አባል መሆንን ያልተቀበሉ ከስራ እየተፈናቀሉና ለስራ አጥነት እየተዳረጉ ናቸው፡፡ የሕዝብ የበቂ ጤናአገልግሎት የማግኘት መብት፤ የተገቢ ትምህርት የማግኘት መብት ወዘተ ተሰርዟል፡፡ ጥቂቶች በብዙሃኑ ላይ አለገደብ

የማግኘትን ዕድል አግኝተዋል፡፡ በምርጫ እንገባለን ያሉትም ቡድኖች ሳይቀሩ የመብት ረገጣው ሰለባ እየሆኑ ናቸው፡፡ የጥቂቶች ህገ ወጥ አገዛዝ በብዙሃኑ ላይ ተጭኗል፡፡ ይህ ሁሉ ኢፍትህዊና መብት ረገጣ ነው፡፡
ስለዚህም ለሰብዓዊ መብት መከበር ሁሉም ዜጋ መታገል ግዴታው ሆኖ ይገኛል፡፡ ሁላችንም በትግሉ እንካፈል፡፡
ኢፖእአኮን እንርዳ!

INJUSTICE ANYWHERE IS INJUSTICE EVERYWHERE
SOCEPP, POSTFACH 51213, BERLIN 13372,GERMANY
SOCEPP, 30 RIGA COVE, WINNIPEG,MB R2P 2Z7,CANADA
E MAIL: SOCEPP @AOL.COM
WEB SITE: WWW.SOCEPP.DE